# አዳምጠኝ ልጄ እምቦቅቅላው




አዳምጠኝ ልጄ እምቦቅቅላው፣
አመት ሳይሞላህ አባ የሆንከው፣
ያሽመገለህ ፍትህ ማጣት ነው፣
ዝናብ ውሃማ እስራኤል የለው!

ልብ በል ልጄ እምቦቅቅላው፣
ጸጉርህ እንደ ጥጥ በኖ የጠፋው፣
አይንህ ጉድጉዶ ዋሻ የሆነው፣
ከሰው ያወጣህ መብት ማጣት ነው፣
የአየር ንብረቱስ ምራቡም ጂል ነው!

አዳምጠኝ ልጄ እምቦቅቅላው፣
አፍህ ኮችሮ ጠጠር የሆነው፣
ጥርስህ ስጋ አንሶት የዘረረው፣
አንጥንትህ ፈጠ የሚቆጠረው፣
አረመኔ ሰው ግጠ በልቶህ ነው፣
የዱር አውሬማ ጃፓንም አለው!

የአንተ እኩያዎች ባውሮጳ ያሉ፣
ኢንተር-ኔት ገብተው እየፈለጉ፣
ጎድኖችህን እየቆጠሩ፣
"አገሩ የት ነው?" ብለው ያዝናሉ!

አዳምጠኝ ልጄ እምቦቅቅላው፣
ቀጭቶ ያስቀረህ ገና ከአበባው፣
ቅልና ዱባው ጣራ ወጥቶ ነው።

ልብ በል ልጄ እቦቅቅላው፣
ሙሉ ገላህን ጠኔ የዋጠው
የሚሰራው ሰው ተሰውሮ ነው፣
ታስሮ ተገሎ ወይ ተሰዶ ነው።

ልብ በል ልጄ እምቦቅቅላው፣
ከፈንና ቀብር የምጠብቀው፣
ነፍሰ-ገዳዩ ክፉ አገዛዝ ነው፣
ዝናብ ውሃማ እስራኤል የለው!

አዳምጠኝ ልጄ እምቦቅቅላው፣
ነፍስህ ልትውጣ በቋፍ ያለችው፣
ህይወት ሲያጣጥር ኑዛዜ ወግ ነው፣
ከገመድ በፊት በላይ እንዳለው፣
ምድሪቱን ሳይሆን ገዥዎን እርገመው፣
ትንፋሽ ካለችህ እንዲህ በላቸው!

"የሚሰሩ እጆች እያሰራችሁ፣
ሐሳቢ አእምሮን እያፎዛችሁ፣
ተሰሚ አንደበት እያፈናችሁ፣
ሕዝብ ጠምዳችሁ እያረሳችሁ፣
ድንቁርናን ዘር እየዘራችሁ፣
እልቂት መከራን እያፈሳችሁ፣
ክህደት ቅጥፈትን እየፈጫችሁ፣
ተንኮል ክፋትን እያቦካችሁ፣
የችጋር ቂጣ እየቀባችሁ፣
ህጻን አዋቂን የገደላችሁ፤
እንኳን ሰማዩ ምድር ይውቃችሁ፣
ያበጥራችሁ እንደ ስራችሁ፣
ገሃነብ ከቶ ይቀቅላችሁ።"

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሰኔ ሁለት ሺህ ዓ.ም.